# ኦሮምኛን ማስፋፋት ሌላ: አማርኛን ማጥፋት ሌላ ነውና ይህ የፀረ አማርኛ ዘመቻ በአስቸኳይ ሊቆም ይገባዋል::

February 6, 2018 – ቆንጅት ስጦታው

ሰሞኑን ኦሮምያ ክልል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ላይ እየተወሰደ ያለው ርምጃ መቆም ያለበት ጉዳይ ነው:: ይህን ስል ኦሮማራ የሚባለውን ነገር (ምናልባት በእውን ያለ ነገር ከሆነ) ያለመፈለግ ወይም የማፍረስ ጉዳይ መስሎ የሚታያቸው ይኖራሉ:: ግን አይደለም:: እኔ የአማራና የኦሮሞን ህዝብ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ወንድማማችነትን አጥብቀው ከሚፈልጉት አንዱ ነኝ::



በኦሮምያ ክልል ለበርካታ ግዚያት ተደጋግሞ ሲታይ የነበረው የጸረ አማርኛ ቋንቋ ዘመቻ ባለፋት ሳምንታት በአዲሱ የኢትዮጵያዊነት አቀንቃኙ ኦህዴድ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ጉዳዩ ኦሮምኛን ማስፋፋት ቢሆን ባልከፋ: ነገር ግን አማርኛን ከክልሉ የማጥፋት ዘመቻ ነው:: ይሄም በሚከተሉት ምክንያቶች ስህተት ነው::

1. ማንኛውም ግለሰብ የመናገር ነፃነት አለው:: የመናገር ነፃነት ደግሞ የፈለጉትን መልዕክት በፈለጉት ቋንቋ ማስተላለፍን ይጨምራል:: የንግድ ታፔላዎችንና ማስታወቂያዎችን በፈለጉት ቋንቋ የመፃፍ መብትንም ያጠቃልላል:: ስለዚህ ይህ የኦሮምያ ክልል መንግስት ርምጃ የፌደራሉንም ሆነ የክልሉ መንግስቶች ህገመንግስቶች እውቅና የሰጡትን የግለሰቦችን የመናገር ነፃነት ይጣረሳል!

2. ይህ የፀረ አማርኛ ዘመቻ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ላይም እየተተገበረ ነው:: በዚህም የተነሳ ዩንቨርሲቲዎች: ባንኮች: የፌደራል መስሪያ ቤት ቅርንጫፎች ወዘተ ከስያሜያቸው ወይም ከማንኛውም አይነት ማስታወቂያና ማሳሰቢያቸው ላይ አማርኛ ቋንቋን እንዲያጠፉና በኦሮምኛ እንዲተኩ እየተገደዱ ነው:: በፌደራል መንግስት ህገመንግስት መሰረት የፌደራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ አማርኛ ሁኖ እያለ እኒህን የፌደራል ተቋማት አማርኛ ቋንቋ መጠቀም አትችሉም ማለት ህገመንግስቱን መጣስ ነው::

3. ይህ ድርጊት በኦሮምያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ከአስር ሚሊየን በላይ አማራዎችን የቋንቋ መብት መንፈግ ነው:: በህገመንግስቱ መሰረት ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን በቋንቋው የመግባባትና ቋንቋውን የማሳደግ መብት ተደንግጎለታል:: ነገር ግን አዲሱ ኦህዴድ የድሮው ኦህዴድ ተቀፅላ የሆነውን የፀረ አማርኛ ፖሊሲውን ተግባራዊ በማድረግ የህዝቦችን ና የግለሰቦችን መብት እየጣሰ ነው::

4. ይህ የፀረ አማርኛ ቋንቋ ዘመቻ በአማራና በኦሮሞ ወንድማማች ህዝቦች ትብብር ላይ ቀዝቃዛ ውሃን የሚቸልስ አካሄድ ነው:: ዘመቻው ወያኔ የሚፈልገውን የሁለቱ ህዝቦችን ፍትጊያና ጥላቻ የሚያሰፋ አካሄድ ነው::

ኦሮምኛን ማስፋፋት ሌላ: አማርኛን ማጥፋት ሌላ ነውና ይህ የፀረ አማርኛ ዘመቻ በአስቸኳይ ሊቆም:ይገባዋል።

